# ለአገር ዘላቂ ጥቅም ማሰብ የአገር ወዳድ መለያ ነው

## ክፍል ሁለት

*አዲስ ቶልቻ 08/25/13*

*ሦስተኛውና የመጨረሻ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ማሣሠቢያ ውስጥ ያለው ሃሳብ፤ አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን የሚመለከት ነው፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚህ ዙሪያ አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሃይማኖትን ሽፋን ካደረጉ ፅንፈኞች ጋር ተቀናጅተው የሃገሪቱን ሰላም ለማወክ እየተንቀሳቀሱ መሆኑን አመልክተው፣ እነዚህ ፓርቲዎች ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ ማስጠንቀቂያ ሠጥተዋል፡፡ ከእነዚህ ፓርቲዎች መሃከል ተጠቃሾቹ ሠማያዊ እና አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ (አንድነት) የተሠኙት ፓርቲዎች ናቸው፡፡*

*እነዚህ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ዓለም አቀፍ መረብ በዘረጉ በመላው ዓለም የጀሃድ ተዋጊዎችንና አሸባሪዎችን በሚደግፉ እስላማዊ የበጎ አድራጎት ድርጅት ተብዬዎች ፔትሮ ዶላር በሚቆረጥለት "ድምፃችን ይሠማ"  የተሠኘ ቡድን ጋር በስውር ተቀናጅተው የሠሩበት ሁኔታ በገሃድ ታይቷል፡፡ ይህም ፓርቲዎቹ በጠሩት የተቃውሞ ሠልፍና አመራሮቹ በየአጋጣሚው በሰጡት መግለጫና ፓርቲዎቹ ባወጡዋቸው ይፋዊ መግለጫዎች የታየ ነው፡፡*

*ሠማያዊ ፓርቲ ግንቦት 25፣ 2005 ዓ/ም  በጠራው የተቃውሞ ሰልፍ ላይ  "ድምፃችን ይሠማ" የተባለው የሠለፊ ዋሃቢ አክራሪ ቡድን አጀንዳዎችን ነበር ያነሣው፡፡ በሠልፉ ላይ የተገኙት ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ በየሣምንቱ አርብ በአንዋር መስጊድና በበኒ መስጊድ እየተገኙ የሚንጫጩ አብዛኞቹ ጉዳዩን በጥልቀት መርምረው የመገንዘብ አቅም የሌላቸው ስሜታዊ ወጣቶች ነበሩ፡፡*

*አንዳንድ ዓለም አቀፍ የመገናኛ ብዙሃን ይህ ሠልፍ ከአገር ውስጥም አልፎ ግዙፉ የዋሃቢ ሠለፊ ቡድን በሆነው ሙስሊም ብራዘር ሁድ የተዘጋጀ እንደሆነ ውስጥ አዋቂ ምንጮችን ጠቅሰው ዘግበዋል፡፡ ለምሳሌ አይል ፕራይስ (oil price) እና ትራምፔት ዶት ኮም (Trumpet .com ) የተሰኙ የዌብ ሣይት መገናኛ አውታሮች "ሰማያዊ ፓርቲ የጠራው የተቃውሞ ሰልፍ በግብጹ ሙስሊም ብራዘር ሁድ ድጋፍ የተዘጋጀ ነው"  ሲሉ ዘግቧል፡፡*

በዚህ ሠማያዊ ፓርቲ በጠራው ሠልፍ ላይ 8 ሚሊዮን ገደማ ሙስሊሞች ቀጥተኛ የድምፅ አሠጣጥ ሥርዓት የተወከለው የእስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት እያለ፣ ይህን የሌለ ያህል የመቁጠር በዓለም አቀፍ የዋሃቢ ሠለፊ የዶላር እርዳታ ጥቂቶች በአወሊያ መስጊድ የመረጠዋቸው ግለሰቦች የሙስሊሙ ተወካዮች እንደሆኑ ተደርጎ ቀርቧል፡፡

የሙስሊሙ ተወካይ ተብዬ ግለሰቦቹ ከውጭ ዶላር የሚልኩላቸውንና ቃል የገቡላቸውን የዋሃቢ ሠለፊ ፖለቲካዊ ርዕዮተ አለም አራማጅ ድርጅቶችን ተገን አድርገው በማን አለብኝነት ዓላማቸውን ለማሣካት ሕገወጥ ድርጊት በመፈፀም ተጠርጥረው ነው በቁጥጥር ሥር የዋሉት፡፡ ይሁንና ሙስሊም ብራዘርሁድና ድምፃችን ይሠማ የተባሉት ሥውር የፖለቲካ አጀንዳ ያላቸው የዋሃቢ ሠለፊ ቡድኖች ከሠማያዊ ፓርቲ ጋር በመቀናጀት በአዲስ አበባ ባካሄዱት ሠላማዊ ሠልፍ ጉዳያቸው በፍርድ ቤት የተያዘው ግለሰቦች የህግ
የበላይነት ተጥሶ በነፃ እንዲለቀቁ ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

በዚህ ሙስሊም ብራዘር ሆድ፣ ድምጻችን ይስማና ሰማያዊ ፓርቲ ተመሳጥረው ባካሄዱት የተቃወሞ ሰልፍ መንግስትን ለማስፈራራት “በቁጥጥር ስር ውለው ለፍርድ የቀረቡት ሰዎች ይፈቱ ለሚለው ጥያቄ መንግስት በሶስት ወራት ግዜ ውስጥ ምላሽ ካልሰጠ ሌላ የተቃውሞ ሰልፍ እንጠራለን” የሚል ማስፈራሪያ አዘል ማስጠንቀቂያ አስቀምጠው ነበር፡፡

በሰላማዊ ሰልፉ ላይ ከዚህም ያለፈ ግልጽ ሕገ ወጥ መፈክሮች ተፎክረውበታል፡፡ ከእነዚህ መሃከል “ ኢቲቪ ሌባ፣ ኢህአዴግ ሌባ” የሚሉት ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ሕገወጥ የሆነ ሰንደቅ ዓላማ የያዙም ነበሩ፡፡ ሕገወጥ መፈክሮቹ ለአንድ አመት ያህል በአክራሪው ቡድን ጀሌዎች ዘንድ የተለመዱ ናቸው፡፡

“እዚህ ላይ አክራሪው የዋሃቢ ሰለፊ ቡድን በኢቲቪ ላይ ለምን የመረረ ተቃውሞ ኖረው?” የሚል ጥያቄ የሚያነሱ መኖራቸው አይቀርም፡፡ እርግጥ ኢቲቪ እንቅስቃሴያቸውን በተመለከተ ያለተፈጠረ፣ ያልታየና ያልተሰማ ዘገባ ስለሚያቀርብ ይሆን? አይደለም፡፡

ማንኛውም አክራሪ እና ወይም አምባገነን ቡድን ሕዝብ ወይም ጀሌዎቹ ከእርሱ እምነት፣ አመለካከትና ፍላጎት ውጭ የሆነ እውነት እንዲያወቁ አይፈቅድም፡፡ ቡድኑ እንደ ጋሪ ፈረስ እይታቸውን ጋርዶ በፈለገው አቅጣጫ ብቻ ሊነዳቸው ነው የሚፈልገው፡፡ በመሆኑም ኢቲቪ የሚያቀርበውን የተለየ ገጽታ ያለው እውነት አዳምጠው ሚዛናዊ የሆነ አቋም የመያዝ እድል እንዳያገኙ ኢቲቪን እርኩስ አድርጎ ያቀርብላቸዋል፡፡

በአክራሪዎችና አምባገነኖች ዘንድ የአመለካከትና የመረጃ አማራጮች የተዘጉ ናቸው፡፡ የሚፈቀደው አንድና አንድ አማራጭ ብቻ ነው፡፡ ወደ ወሃቢ ዋሃቢ ሰለፊ ስንመለስ ቡድኑ የሚመራበት አመለካከትና ቡድኑ አመለካከቱን የበላይ አድርጎ ለማንገስ የሚከተለው አቅጣጫ ብቻ ነው የሚፈቀደው፡፡ ከዚህ የተለየ አመለካከትና አቋም ውጉዝ ነው፡፡ ድምጻችን ይሰማ የተባለው በውጭ ኃይል ገንዘብና አይዞህ ባይነት የሚመራው የወሃቢ ሰለፊ ቡድን የሚያሰማው "ኢቲቪ ሌባ" የሚል መፈክር መነሻ ይህ ነው፡፡

ሰማያዊ ፓርቲ ከአክራሪዎቹ ጋር ጥምረት ፈጥሮ 5 ሺህ ያህል የአክራሪውን ጀሌዎች ለሰልፍ አውጥቶ "ደጋፊ አለኝ" ለማስባል ያካሄደውን የተቃውሞ ሰልፍ የተመለከተው አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲም ከመድረክ ፓርቲዎች በተፋታ ማግስት የአክራሪ ዋሃቢ ሰለፊ ጀሌዎችን ተማምኖ የተቃወሞ ሰልፍ ጠርቷል፡፡ በዚህ መሰረት በተለይ ዙሪያዋ የአክራሪዎች መፈንጫ ሆና በቆየችው፣ ሃረከቱል ሸባብል ፊ ቢላል ሂጅራይተን የተባለው አልሸባብ አልቃይዳ ባሰለጠናቸው ግለሰቦች ይመራ የነበረ የዋሃቢ ሰለፊ የጀሃድ ቡድን ማእከሉ ሊያደርጋት በሞከረባት የደቡብ ወሎ ዞን ዋና ከተማ ደሴ በሺህ የሚቆጠሩ የአክራሪ ጀሌዎችን አደባባይ ማወጣት ችሏል፡፡

በዚህ የተቃውሞ ሰልፍ ላይ የድምጻችን ይሰማ የዋሃቢ ሰለፊ እንቅስቃሴ ቡድን ፈጣሪ የሆኑትና ራሳቸውን " የሙስሊሙ ተወካይ" ብለው ይጠሩ የነበሩት ግለሰቦች በወንጀል ተጠርጥረው የተከሰሱበትን የጸረ ሽብተኝነት ሕግ ይሰረዝ የሚል መፈክር ለማስተጋባት ተሞክሯል፡፡

በመላው ኢትዮጵያ፣ በአበዛኛው የኦሮሚያ አካባቢ፣ በተወሰኑ የትግራይ፣ የአማራ፣ የደቡብና የቤኒሻንጉል ክልሎች አካባቢዎች፣ ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል ሁኔታ የሙስሊሞች መኖሪያ በሆኑት የሶማሌ፣ የአፋርና የሃራሬ ክልሎች የሚኖሩ ሙስሊሞች ከነመኖራቸውም የማያውቋቸውና በወንጀል ተጠርጥረው የፍርድ ሂደታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙ አስራሰባት ግለሰቦችን " የሙስሊሙ ተወካዮች" አድረጎ በማቅረብ "ይፈቱ" የሚል ፉከራም ተሰምቷል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በዚያው በደሴ ከተማ በአክራሪ የወሃቢ ሰለፊ ቅጥረኞች ሕይወታቸው ያለፈውን የሼሕ ኑሩ ይማም ግድያ ጉዳይ ለማደናገር "ግድያው ድራማ ነው" የሚልና በአክራሪ ዋሃቢ ሰለፊዎች ዘንድ የተለመደው "ኢቲቪ ሌባ" የሚሉ ጸያፍ ጩኸቶችም ተሰምተዋል፡፡

ልክ እንደሰማያዊ ፓርቲ ሁሉ አንድነት በደሴ በጠራው ሰላማዊ ሰልፍ ታዳሚዎች ሙሉ በሙሉ የዋሃቢ ሰለፊ አክራሪዎች ጀሌዎች ናቸው፡፡ አንድነት ግን እነዚህን ሆን ብሎ የተጣመራቸውን

የአክራሪ ጀሌዎች ፓረቲውን በፖለቲካ አመለካከቱ የሚደግፉ ዜጎች አስመስሎ ሊያቀርብ ሞክሯል፡፡ ይሁን እንጂ በተመሳሳይ እለት  የዋሃቢ ሰለፊ አክራሪዎች መሰረት በሌላቸው ጎንደር ከተማ ላይ፣ ከሳምንታት በኋላ በአርባምንጭና በጂንካ ከተሞች  ባጠራቸው የተቃውሞ ሰልፎች ላይ ከ50ና 60 የማይበልጡ ሰዎች መገኘታቸው የደሴው የተቃውሞ ሰልፍ ታዳሚ የአንድነት አመለካከትና ፖሊሲዎች ደጋፊዎች ሳይሆኑ የራሱ ፖለቲካዊ ግብ ያለው የዋሃቢ ሰለፊ አክራሪ ቡድን ደጋፊ ጀሌዎች መሆናቸውን ገሃድ አውጥቷል፡፡

ሁኔታውን በአንክሮ የታዘቡ ዜጎች አንድነት ከዚህ የተቃውሞ ሰልፍ አንዳችም ያተረፈው ነገር እንደሌለ ተገንዝበዋል፡፡ ሰላም ወዳዱ የኢተዮጵያ ህዝብ አንድነት ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት እስላማዊ መንግስት የመመስረት ስትራቴጂ ይዞ የሚንቀሳቀሰውን የዋሃቢ ሰለፊ አክራሪ ቡድን አቋሞች በማስተጋባቱ ፓርቲው ለኢትዮጵያ ህዝብ ዘላቂ ሰላምና ጥቅም ደንታ የሌለው ነው ሲሉ በእጅጉ ታዝበውታል፡፡ በተለይ ተጠርጣሪዎቹ ሳምንታት ባልፈጀ ግዜ ውስጥ በቁጥጥር ስር የዋሉበትንና ይህም በይፋ የተገለጸውን የሼህ ኑሩ ይማም ግድያ በተመለከተ በአደባባይ “ግድያው ድራማ ነው” እያስባለ ማሸለሉ ብዙዎችን ብእጅጉ አሳዝኗል፡፡

በተለይ ከሼህ ኑሩ ግድያ ጋር ጋር በተያያዘ በፓርቲው አማካኝነት የተንጸባረቀውን ጸያፍ ነገር ሕዝቡ እንዳልወደደው የተረዱ የአንድነት አመራሮች ራሳቸውን ነፃ ለማድረግ፣ “ፓርቲያችንን ከሼህ ኑሩ ግድያ ጋር ማገናኘት ተገቢ አይደለም” ሲሉ ተደምጠዋል፡፡ የሚገርመው አንድነትን ከሼህ ኑሩ ግድያ ጋር ያገናኘው ሕዝብ ወይም መንግስት አይደለም፡፡ አንድነት ራሱ እንጂ፡፡ በቅድሚያ በደሴ በጠራው ሰላማዊ ሰልፍ ላይ አክራሪዎቹን ከተጠያቂነት ነጻ ለማሰኘት “ግድያው ድራማ ነው” እያስባለ በአደባባይ ያስሸለለው አንድነት ራሱ ነው፡፡

ከዚህ በኋላ በጠራችሁት የተቃውሞ ሰልፍ ላይ “ ‘ግድያው ድራማ ነው’ የሚል መፈክር መሰማቱ ተገቢ ነው ወይ?” ተብሎ ሲጠየቁ የፓርቲው ከፍተኛ አመራር አቶ አስራት ጣሴ በሰጡት ምላሽ “ማስረጃው ታዲያ የት አለ!?” የሚል መከራከሪያ አቅርበዋል፡፡ ይህ የአቶ አስራት ጣሴ መከራከሪያ በጉዳዩ ላይ አክራሪው ቡድን የያዘውንና በጠሩት የተቃውሞ ሰልፍ ላይ የተሰማውን መፈክር እንደሚደግፉት ያሳያል፡፡

አንድነት በዚህ አኳኋን ራሱን ከሼህ ኑሩ ግድያ ጋር በማጣመሩና ሌሎች የአክሪውን ቡድን አላማዎች በማስተጋባቱ ነው ሕዝብና መንግስት ከቡድኑ ጋር ተጣምረው መንቀሳቀሳቸወን የተገነዘቡት፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ “አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከፅንፈኞች

ጋር ጥምረት መስርተዋል” የሚል አቋም ይዘው ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ ማስጠንቀቂያ እንዲሰጡ ያደረጋቸውም ይህ ተጨባጭ እውነታ ነው፡፡

በውጭ የሚኖሩ ተቃዋሚዎችም አክራሪውን ቡድን ለመደገፍ ሽሚያ የገቡ ይመስላሉ፡፡ እነዚህ አሜሪካና አውሮፓ በርገራቸውን እየገመጡ የሸፈቱ “ተቃዋሚ ነን” ባዮች ገሚሱ ድሮ ሞቶ ተቀብሮ ያበቃለትን የአንድ ብሄር የበላይነት የሰፈነባትን አሃዳዊ ኢትዮጵያ የመኒናፍቁ ያፈጁና ያረጁ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጰያዊያን ናቸው፡፡ ሌሎቹ ከሕዝበ ፍላጎትና ፍቃድ ውጭ ብሄሮችን ገንጥለው እንደፈለጉ በአምባገነንነት የሚፈነጩበት ግዛት የመፍጠር ሕልም ያላቸው ናቸው፡፡ የተቀሩት ደግሞ በተለያየ መነሻ በኢትዮጰያ ሕገመንግስታዊ ስርአትና ገዢው ፓርቲ ላይ ጭፍን መሰረተ ቢስ ጥላቻ (prejudice) ያደረባቸው፣ በዚህ ምክንያት ኢትዮጵያን ዳግም አገር ልትሆን በማትችልበት ሁኔታ ለማተራመስ እንቅልፍ አጥተው የሚባዝኑ፣ ሻአቢያን የመሳሰሉ የኢትዮጵያ ጠላቶችን በቅጥረኝነት የሚያገለግሉ ናቸው፡፡

እነዚህ ቡድኖች የዋሃቢ ሰለፊ አክራሪዎች እንቅስቃሴ መንግስትን አንበርክኮ ወደስልጣን የመምጣት፣ እገር የመገንጠል፣ ኢትዮጵያን የማጥፋት ሕልማችንን ያሳካል በሚል አክራሪውን ቡድን ጎምጅተውታል፡፡ በተለያየ መንገድ ድጋፋቸውን እየገለጹለት ይገኛሉ፡፡ ተበድያለሁ በሚል ለሚያሰማው ባዶ ጩኸት ተገቢነት ማረጋገጫ ለመስጠት እየሞከሩም ነው፡፡

የአክራሪውን ቡድን እንቅስቃሴ በሚደግፉት የውጭ የአሜሪካና አውሮፓ ከተሞች ሽፍቶች መሃከል ተነገረ የተባለውንና ከወደ ሰሜን አሜሪካ የሰማሁትን አንድ ወሬ ላንሳላችሁ፡፡ ይህም “አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው መንግስት የአንድ ብሄር የበላይነት ያለበት ነው፡፡ ስለዚህ አክራሪው ቡድን የሚያሰማውን ተቃውሞ መደገፍ አለብን” የሚል አሮጌ ወሬ ነው፡፡

ይሀ አስተሳሰብ አንድ ስለ አዲሲቷ ኢትዮጵያ ምንም ካለማወቅ የመነጨ፣ ሁለት የአንድ ብሄር የበላይበት የነበረባትን የቀድሞዋን ኢትዮጵያ የሚናፍቀ የአሮጌው ስርአት ርዝራዦች አስተሳሰብ ነው፡፡ በመሰረቱ የአሁኗ ኢትዮጵያ በብሄር ላይ የተመሰረተ ፌደራላዊ አወቃቀር ያላት አገር ነች፡፡ እያንንዳንዱ ብሄር ራሱን በራሱ ነው የሚያስተዳድረው፡፡ ትግሬው ኦሮሞውን አማራው ጋምቤላውን፣ ሶማሌውን አማራውን … አያስተዳድሩም፡፡

ስለዚህ አንድ ወይም ሁለት ብሄሮች በበላይነት የሚያሰተዳድሯት አገር ነች ሊያስብል የሚችል ነገር የለም፡፡ ይሀ ሁኔታ በሕገመንግስቱ ተዘገታል ፡፡ በብሄር ብሄረሰቦች አሰፋፈር ላይ በመመሰረት የተዋቀሩት የክልል ግዛቶች የፌደራል መንግስቱ የስልጣን ምንጭ ናቸው፡፡ ፌደራል

መንግስቱን የመሰረቱት ብሄራዊ ክልሎቹ ናቸው ፡፡ የፌደራል መንግስት ስልጣን ከክለሎች የመነጨ ነው፡፡ በዚህ የፌደራል መንግስት ውስጥ ትልቁ የስልጣን አካል የሆነው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እነደየሕዝብ ብዛታቸው ከሁሉም ክልሎች የተወከሉ አባላትን የያዘ ነው፡፡

ተጠሪነቱ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሆነው በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራው ስራአስፈጻሚም ከሁሉም ብሄሮች - ክልሎች የተወጣጡ ባለስልጣናት የተካተቱበት ነው፡፡ እንግዲህ “ኢትዮጵያ የአንድ ብሄር የበላይነት የሰፈነባት ነች” በሚል የወሃቢ ሰለፊ አክራሪዎች መንግስት ገልብጠው የአንድ ሃይማኖት የበላይነት የሰፈነባት መንግስት እንዲመሰርቱ መጎምጀት ምን የሚሉት እብደት ነው?

በአጠቃላይ ሰፊው ሰላም ወዳድ የኢትዮጵያ ህዝብ የዋሃቢ ሰለፊ አክራሪዎቹን አካሄደ በሚገማ ተገንዝቧል፡፡ ለአገሪቱ ዘላቂ ሰላምና ልማት አደገኛ መሆኑንና በእኝጭጩ መቀጨት እንዳለበትም ያምናል፡፡ አንዳንድ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች አመቺ ሆኖ ሲያገኙት የሚንጠለጠሉበትን ሕገ ወጥ የመንግስት ለውጥ የማምጣት ሕልም ያሳኩልናል በሚል ከአክራሪዎቹ ጋር መጣመራቸውንም እጅግ ተፀይፎታል፡፡

በመሆኑም ባለማወቅ አክራሪውን ቡድን የደገፉ የዋሕ ዜጎችና ከአክራሪው ጋር የተጣመሩ ተቃዋሚ ፓርቶች ለኢተዮጵያ ዘላቂ ሰላምና ልማተ በማሰብ አካሄዳችሁን እንድታስተካክሉ ሕዝብ ያሳስባል፡፡ ለአገር ዘላቂ ጥቅም ማሰብ የአገር ወዳዶች መለያ ነውና፡፡